# በኢትዮጵያ የሥርዓተ-ፆታ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ እና የትግበራ ሂደቶች

NEWA
ICTJ Justice Truth Dignity
german cooperation
Implemented by giz
Co-funded by the European Union

## የፖሊሲ አጭር መግለጫ

## በኢትዮጵያ የሥርዓተ-ፆታ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ እና የትግበራ ሂደቶች

### 1. መግቢያ እና አስፈላጊነት

በሽግግር ፍትህ ውስጥ የስርዓተ-ፆታ አመለካከትን ማካተት መሰረታዊ ፍትሃዊነትን እና የሰብአዊ መብቶች መከበርን እንደማረጋገጥ ይወሰዳል። ማንኛውም የሽግግር ፍትህ ስርዓት ስርዓተ-ፆታን በማካተት፣በሂደቱም ውስጥ በመጠቀም፣ እንዲሁም ፖሊሲዎችን በመቅረፅ እና በማስፈፀም የሴቶችን እኩል ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ያስችላል። ይህ አካሄድ ቀልጣፋ እና ወጪ ቆጣቢ ብቻ ሳይሆን ሴቶች በግጭቶች እና በፍትህ እጦት ጭምርም ይበልጥ ተጎጂ በመሆናቸው አስፈላጊ ያደርገዋል። በመሆኑም ሴቶችን ከሽግግር የፍትህ ሂደት ማግለል የሁሉንም ተጎጂዎች ፍላጎት በበቂ ሁኔታ ምላሽ መስጠት ስለማያስችል ወይም ለሰፊው የህብረተሰብ ለውጥ የበኩሉን አስተዋጽኦ ስለማያደርግ ለስኬታማነቱ እንቅፋት ይሆናል። በህብረተሰብ ውስጥ በወንዶች እና በሴቶች መካከል ፍትሀዊ የስልጣን እና የመብት ክፍፍል አለመኖሩን በመገንዘብ የሥርዓተ-ፆታ ሽግግር ፍትህ ተገቢ የሆኑትን ዘዴዎች መከተል ይጠይቃል፡ ፡ በኢትዮጵያ ውስጥ በእያንዳንዱ የፖሊሲ ቀረፃና ትግበራ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ለዘመናት የተገለሉ ወገኖችን ድምጽ፣ ፍላጎት፣ እና መብት በማካተት እውነተኛ ፍትህ እንዲሰፍን ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

የሥርዓተ-ፆታ አመለካከትን በሽግግር ፍትህ ውስጥ ማካተት፣ ብዙውን ጊዜ ‹የሽግግር ፍትህ› እየተባለ የሚጠራ ሲሆን፣ የተለያዩ አቀራረቦችን ያካትታል። እነዚህም ሴቶች በብሔራዊ የፍትህ ሽግግር ማዕቀፍ ውስጥ እንዳይካተቱና እንዲገለሉ ይደረግ የነበረውን አሰራር በማስቀረት ለመደበኛ የእርቅና የመልሶ ግንባታ ሂደቶች አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ አስቻይ ሁኔታን ይፈጥራል። ሌላው አካሄድ ደግሞ ሴቶች የደረሰባቸውን የተለያዩ የጉዳት ዓይነቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት እና ልዩ የመፍትሄ ፍላጎቶቻቸውን በማስተናገድ ላይ ያተኩራል። ይህ አካሄድ ከስርዓተ-ፆታ ጋር የተያያዙ ኢ-ፍትሃዊ ድርጊቶችን በሽግግር ፍትህ አውድ ውስጥ ለመፍታት እና ለማስተካከል ይሻል። የስርዓተ-ፆታ አመለካከትን ወደ ሽግግር ፍትህ ማካተት ለፍትሃዊነት እና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ፋይዳ አለው። ለምን ቢባል ሴቶች በፖሊሲ ልማት እና ትግበራ ውስጥ ሊኖራቸው የሚገባውን እኩል ተሳትፎ ስለሚያረጋግጥ፡ እንዲሁም ለጥቃት ተጋላጭነታቸውንና በግጭቶች ወቅት የሚደርስባቸውን ችግር እና የመብት ጥሰቶች እንዲቀንስ ስለሚያግዝ ነው፡፡ ይህ የስርዓተ-ፆታ አካሄድ ሰላምን ለማስጠበቅ እና ተደጋጋሚ የጥቃት ዑደቶችን ለማስቆም ሁነኛ ዘዴ ነው ተብሎ ይታመናል። እንዳይደመጡ የተደረጉ ድምፆችን እና ፍላጎቶቻቸውን ለማካተት ዘዴዎችን ማበጀት እንዲሁም ገሀድ ለሆነው የኃይል ሚዛን አለመመጣጠን ትኩረት መስጠትን ይጠይቃል። እነዚህ ሥርዓተ ፆታን ያማከሉ ጥረቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ሴቶች ከብሔራዊ የሽግግር ፍትህ ሂደቶች መገለላቸውን የሚያስተካክሉ ሲሆን በሴቶች ላይ የሚደርሰውን በደል በማካካስ ለመፍታት ያስችላል።

### 2. የፖሊሲው አቀራረብ እና ዓላማዎች

በኢትዮጵያ ውስጥ በሴቶች ላይ የሚሰነዘሩ አድሎአዊ ድርጊቶች እና አመለካከቶች ለሴቶች ህዝባዊ ተሳትፎ ዋና እንቅፋት እንደሆኑ እና በዚህም የተነሳ መብቶቻቸው እንደሚጣሱ የተለያዩ ጥናቶች ያመለክታሉ። እ.ኤ.አ. በ2021 የተደረገ ጥናት እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ወንድ የፖለቲካ መሪዎች የሴቶችን የፖለቲካ አመራር በተመለከተ የሴቶች ተሳትፎ እና ውጤታማነት ላይ አሉታዊ አመለካከቶች ሲኖራቸው በህግ አውጪ እና በአስፈጻሚነት ቦታ ላይ ያሉ ሴት የፖለቲካ መሪዎች ደግሞ ሴቶች በመንግስት እና በፖለቲካ አመራር ውስጥ ስለሚኖራቸው ተሳትፎ የበለጠ አዎንታዊ አመለካከቶችን አሳይተዋል፡፡ እነዚህ አመለካከቶች በተለይም በፖለቲካ እና በማህበረሰባዊ አመራር ውስጥ የተባእታይ ፆታ የበላይነትን ከሚያበረታታው ባህል እና ማህበራዊ ስሪት የመነጩ ናቸው። የኢትዮጵያ ተለምዶአዊ አስተሳሰቦችና ድርጊቶች ሴቶችን የማህበረሰብ ወይም የፖለቲካ ተወካይ አድርጎ ከማቅረብ ይልቅ የቤት ዉስጥ አገልጋይ ብቻ አድርጎ ወደማየት ያዘነብላል። ይህ የሥርዓተ-ፆታ አድልዎ የተመሰረተው ህብረተሰቡ ወንዶች የበላይ ውሳኔ ሰጪዎች መሆናቸውን በመቀበሉ ሲሆን ሴቶች ብዙውን ጊዜ ጥገኛ እና ታዛዥ ሆነው ስለሚታዩ የፖለቲካ ተሳትፏቸው እና ተጽኖአቸው ውስን እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ አንዳንድ መሻሻሎች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቢታዩም ሴቶች በህብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ዘርፎች ውስጥ በርካታ ችግሮች እና መገለሎችን ማስተናገዳቸው እንደቀጠለ ነው።

ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ. በ2018 ሀገራዊ ምክክር፤ ብሔራዊ እርቅ እና ዘላቂ ሰላምን ጨምሮ ቁልፍ ሀገራዊ የማሻሻያ እንቅስቃሴዎችን የጀመረች ሲሆን በዚሁ ወቅት ሀገሪቱ አስከፊ የእርስ በርስ ጦርነት እና በርካታ የአካባቢ እና ክልላዊ ግጭቶችን አስተናግዳለች። ከዚህ ጋር በተያያዘ እ.ኤ.አ. በህዳር 2022 በፕሪቶሪያ የሰሜኑን ጦርነት ለማስቆም ያስቻለ የተኩስ-አቁም ስምምነት በፌዴራል መንግስት እና በህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) መካከል ተፈርሟል፡፡ በስምምነቱም ላይ የሽግግር ፍትህ ጉዳይ በጉልህ የተጠቀሰ በመሆኑ፣ የፌደራል መንግስቱ ሁሉን አቀፍ የሽግግር የፍትህ ፖሊሲ፣ በአገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉ ልምዶችን በማካተት እንቅስቃሴ ጀምሯል። በዚህም መሰረት የፍትህ ሚኒስቴር ‘የኢትዮጵያ የፖሊሲ አማራጮች ለሽግግር ፍትህ፣ረቂቅ ለባለድርሻ አካላት ምክክር ጥር 2023’ በተለምዶ “the Green Paper” ተብሎ የሚጠራውን የፖሊሲ ንድፍ ኣቅርቧል። በተፈጠረው መድረክ ላይም ተጎጂዎችና የሲቪል ማህበራት ተቀዳሚ ትኩረት በሚገባቸው የፍትህ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን እንዲገልጹ እድል ከመስጠት ባሻገር ይዳብረ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ በመቅረፅ አሳታፊ ሂደትና ዘላቂ ውጤት ለማምጣት መሰረት የሚጥል ሁኔታ መፍጠር ተችሏል። “the Green Paper” በርካታ ጉዳዮችን ይዳስሳል፣ አማራጮችንም ይጠቁማል፣ እንዲሁም የያንዳንዱን ኣማራጭ ጥቅሞች እና ጉዳቶቹን ኣስመልክቶ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ይሰጣል። ነገር ግን ግርድፍ ትንታኔዎች እንደሚያሳዩት ስለ ፖሊሲው የተደረጉ ክርክሮች በሥርዓተ-ፆታ ምልከታ የተቃኙ ኣይደሉም ። በሌላ በኩል ጉዳዩን ጠለቅ አድርገን ስንመለከተው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲዉን በሥርዓተ-ፆታ መነፅር መልሶ ማየት አስፈላጊ መሆኑን አንረዳለን።

በዚ ጉዳይ የዓለም አቀፉ የሽግግር ፍትህ ማዕከል (ICTJ) እና የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ተሟጋች ኮንሰርቲየም (CEHRO) በአውሮፓ ህብረት በሚደገፈው “የሲቪል ማህበራት በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ሂደት ላይ ኣሰተዋፆ ይኖራቸው ዘንድ አቅማቸውን ማጠናከር” በተሰኘው ፕሮጀክታቸው (CoSAP) , እና (NEWA) ከተሰኙ ሁለት አንጋፋ የሀገር አቀፍ የሴቶች መብት ድርጅቶች ጋር በመተባበር ሰርተዋል። በዚ መሰረት NEWA የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከቶችና በሁሉም አካባቢዎች የሚኖሩ ሴቶች አንድ ላይ በማምጣት በሽግግር ፍትህ ዙርያ ተከታታይ ስልጠናዎችን በመስጠት ለሴቶች ሁለንተናዊ እድገት መጠናከር በኢትዮጵያ ሥርዓተ-ፆታ ተኮር የሆነ የፍትህ ሽግግር ፖሊሲ ግብአት እንዲሰጡ አና በዚ ጉዳይ ላይ የጥብቅና ድምፃቸው እንዲጎለብት ኣድርጋለች።

### 2.1. አቀራረብ፤ ባለ ሁለት ደረጃ የአቅም ግንባታ ምክክሮች

ይህ የፖሊሲ ምክረ ሃሳብ ሰነድ በኢትዮጵያ ለሥርዓተ-ፆታ የሽግግር ፍትህ ወሳኝ ግምገማ እና ምክክሮች ላይ የተመሰረተ ሲሆን በማጠቃለያውም የሽግግር ፍትህ ስልቶች እርስ በርስ ተሰናስነው እንጂ በተናጠል መታየት እንደሌለባቸው አፅንኦት ሰጥቷል። ለሽግግር ፍትህ ሁሉን አቀፍ አቀራረብ አስፈላጊነትን አጉልቶ ያሳያል፣ እያንዳንዱ አሰራር ተደጋግፎና ተመጋግቦ የሚቀርብበት፣ ኢ-ፍትሃዊ በደሎችን ለመቅረፍ የሚያስችል ሁለገብ እና ውጤታማ አሰራር ነው። በዚህም መሰረት ይህ የፖሊሲ ምክረ ሃሳብ ከሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች ከተወጣጡ የማህበረሰብ ተወካዮች እና ልሂቃን ጋር በተደረጉ ውይይቶች ከተገኙ መሰረታዊ እና ወሳኝ ጉዳዮችን በማካተት በሁለት ዘርፍ ሂደቶች የተዘጋጀ ነው።

የCoSAP እንቅስቃሴ ከኦሮሚያ እና ሶማሌ ክልል የተውጣጡ ከ150 በላይ ሴቶችን በማህበረሰብ አቀፍ ምክክር ያሳተፈ ሲሆን ምክክሮቹ ያለፉትን እና ውቅታዊ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በተመለከተ መሰረታዊ የሴቶችን ቅሬታዎች፣ ጥያቄዎች እና ፍላጎቶች ግልጽ ለማድረግ እና ግንዛቤ ለማስጨበጥ አግዘዋል። ተሳታፊዎቹም በተለይም መደበኛዉ የፍትህ ስርዐት ለሴቶች ያለዉን የተደራሽነት ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት ድሃ ሴቶች ወደ መደበኛው የሽግግር ፍትህ ሂደት ተሳታፊ በሚሆኑበት አካሄድ ላይም መክረዋል።

በነዚህ ግብአቶች ላይ በመመስረት NEWA ከICTJ ጋር በመተባበር የሽግግር ፍትህ ፅንሰ-ሀሳቦች ላይ የተጠናከረ ቴክኒካል ስልጠናዎችን

በተለይም የስርዓተ-ፆታ ስልቶችን እና የምክክር መድረኮችን በማዘጋጀት ለሁለት ቀናት የሚቆይ አጭር የፖሊሲ የፅሁፍ አውደ ጥናት (policy brief writing workshop) አካሂዳለች። በአውደ ጥናቱም ላይ ከሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች የተውጣጡ የሴቶች ማህበራት፣ ከማህበረሰቡ የተወከሉ ሴቶች እና የሥርዓተ ፆታ ባለሙያዎች ተሳትፈውበታል።

## 2.2. የፖሊሲው ዓላማዎች

ይህ አጭር የፖሊሲ መግለጫ የፍትህ ሚኒስቴር ለሽግግር ፍትህ የስራ ቡድን (TJWG) “green paper” ለባለድርሻ አካላት ምክክር ባቀረበበት ወቅት በተሰጠው ሰፊ ግብአት ላይ ትኩረቱን አድርጓል። እንዲሁም ከUN ከተወጣጡ ሴቶች ጋር በመተባበር የፖሊሲ አማራጮች ላይ ለመወያየት በTJWG በከፍተኛ ደረጃ ብቸኛ የሴቶች ብሔራዊ መድረክ እንዲገነባ አድርጓል። ሁለቱም ICTJ እና NEWA በብሔራዊ መድረክ ላይ ተሳትፈዋል:: ICTJ በሽግግር ፍትህ ላይ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮችን በተመለከተ ጠቅለል ያለ እይታ አቅርቧል።

ይህ የፖሊሲ ገለፃ የTJWG “Green Paper” ስርዓተ-ፆታ በመጠቀም እና ሥርዓተ-ፆታን በሚነካ መልኩ ወሳኝ ትንታኔ እና ገንቢ አማራጮችን አቅርቧል። የኢትዮጵያን ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ እና ታሪካዊ ብዝሃነት የሚስማማ፣ ሴቶች የሚያጋጥሟቸውን ልዩ ልዩ ተግዳሮቶች የሚፈታ፣ በሚገባ የተብራራ የሥርዓተ-ፆታ ተኮር የፖሊሲ ማዕቀፍ እንደሚያስፈልግ አስቀምጧል። የሴቶችን ድምጽ እና ልምድ የማካተት አስፈላጊነትን በየደረጃው የሚገኙ ፖሊሲ አውጭዎችን፣ የፍትህ ሚኒስቴር የሽግግር ፍትህ የስራ ቡድን (TJWG) እንዲሁም ህብረተሰቡን ለማስገንዘብ ሁለገብ የሆነ ሥርዓተ-ፆታን በግልፅ እና በዘላቂነት የሚመራ የተሻሻለ ፖሊሲ እና የስርዓተ-ፆታ አሰራርን ያቀርባል።

ይህ የፖሊሲ ማጠቃለያ “በGreen paper” ስምምነት እና ፖሊሲ አውጪዎች ላይ ተጽእኖ ከማሳደር በተጨማሪ ውጤታማ እና ዘላቂነት ያለው ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር የሽግግር የፍትህ ሂደቶች እና አተገባበር ላይ የተለመዱ ስልቶችን በማስገንዘብ ተቆርቋሪነትንና እና ህዝባዊ ምክክርን ለማጎልበት ያለመ ነው።

# 3. በኢትዮጵያ የሽግግር የፍትህ ሂደት ውስጥ የስርዓተ–ፆታ መርሆዎች እና ቋንቋን ማካተት፤ አጠቃላይ እይታ

ጠንካራ ሥርዓተ-ፆታን ያካተተ የሽግግር የፍትህ ፖሊሲ በርካታ የመብት ጥሰቶች የሚደርሱባቸውን ሴቶች እና የተገለሉ ቡድኖችን እንደ ልዩ የትኩረት ቡድን እውቅና በመስጠት ሰፋ ያለ አድማስ እንዲኖረው ይጠበቃል። ከሥርዓተ-ፆታ በተጨማሪ እንደ እድሜ፣ ጎሳ፣ አካላዊ ጤንነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሁሉን አቀፍ፣ ተለዋዋጭ፣ ለአዳዲስ አቀራረቦች ዝግጁና ተደራሽ መሆን ይኖርበታል። እነዚህ አካሄዶች በፖሊሲው ውስጥ መካተትና መዳበር አለባቸው:: ተግባራዊነቱን ለመከታተል፣ ለመማማር እና እንደ አስፈላጊነቱ ለማሻሻል የሚረዱ ዘዴዎችን በውስጡ አቅፏል። በተጨማሪም ኢትዮጵያውያን ሴቶች በየደረጃው ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉበትን አሰራር በመዘርጋት፣ በፖሊሲ ቀረፃ ሂደት ይደርስባቸው የነበረውን መገለል በመቅረፍ ልዩ ልምዳቸውን፣ ፍላጎቶቻቸውንና አቅማቸውን በማዳበር ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባዋል። ይህ አካሄድ በስርዓተ-ፆታ ኮታ ብቻ የተገደበ ሳይሆን የሴቶችን ውጤታማ ውክልና ለማረጋገጥ በአቅም ግንባታ፣ በልዩ ስልጠና እና በባለሙያዎች አመዳደብ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይኖርበታል።

የኢትዮጵያ የሽግግር የፍትህ ፖሊሲ የግጭት፣ የጦርነት እና የሰብአዊ መብት ጥሰት መዘዝ በሴቶች ላይ ያላቸውን አሉታዊ ተፅእኖዎች ዘርፈ-ብዙ መሆናቸውን በማያሻማ ቋንቋ ማቅረብ አለበት። እነዚህ የተለያዩ የመብት ጥሰቶች በብሔራዊ የሽግግር የፍትህ ሂደት ውስጥ ተዘግበው እንዲፈቱ ማድረግ ያስፈልጋል። የአፍሪካ ህብረት የሽግግር የፍትህ ፖሊሲ (AUTJP) (AUTJP) መርሆዎች እና ቋንቋ የስርዓተ-ፆታን ጉዳይ ከግምት ከማካተት አንፃር ሁሉን አቀፍ ናቸው ተብሎ መውሰድ ይቻላል። የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ እንደ አፍሪካ አንድነት አህጉራዊ ፖሊሲ ተመሳሳይ መርሆችን እና ቋንቋን በመከተል ጠንካራ ሊሆን ይገባዋል።

AUTJP የሴቶችን እና የልጃገረዶችን ሁኔታ፣ እንዲሁም የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮችን በአፍሪካ , ውስጥ እንደ ተሻጋሪ የሽግግር ፍትህ ጉዳዮችን በማስቀመጥ የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ በማፅደቅ የተሟላ ይሆናል።

ከAUTJP በተጨማሪ ኢትዮጵያ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት መርሆዎችን የሚያጠቃልሉ ቁልፍ የሆኑ ዓለም አቀፍ የፖሊሲ ማዕቀፎችን እና የሕግ ስምምነቶችን አፅድቃ ተቀብላለች። ፖሊሲ አውጪዎች እንደ ብሔራዊ የሰብአዊ መብት ተቆርቋሪ ሆነው እነዚህን ስምምነቶች በሀገሪቱ ህገ-መንግስት መሰረት የማክበር ግዴታ አለባቸው። የሚከተሉት ቁልፍ ስምምነቶች እንደ ማጣቀሻ እና የመመሪያ ምንጭ ሆነው ሊያገለግሉ ይገባል፡-

- ኢትዮጵያ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ማንኛውንም አይነት አድልዎ ለማስወገድ በ1981 ያፀደቀችው ኮንቬንሽን (CEDAW)።
- ኢትዮጵያ በ2018 ያፀደቀችው በአፍሪካ የሴቶች መብት (2003) የተከሄደውን የአፍሪካ የሰብአዊና የህዝቦች መብቶች ቻርተር (ACHPR)
- የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ (UNSCR) 1325/2000 እና የሚከተሉት የውሳኔ ሃሳቦች በሴቶች፣ ሰላም እና ደህንነት (WPS) ዙሪያ ሲሆን ኢትዮጵያም የተቀበለችው ሲሆን የWPS አጀንዳ የትጥቅ ግጭት በሴቶች ላይ የሚያደርሰውን ተፅእኖ በመገንዘብ እና ሴቶች በሰላም ግንባታ ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ እንዲያደርጉ እንዲሁም ሰላምን እና ደህንነትን ለማጎልበት የሚደረገውን ጥረት ሁሉ ለመደገፍ በመሆኑ ዋቢ ለማድረግ አጋዥ ነው።

# 4. የሥርዓተ–ፆታን ከግምት ውስጥ በማስገባት እውነትን መፈለግ

ከእውነት ፍለጋ ሂደቶችና መስፈርቶች መካከል ለሰብአዊ መብት ጥሰቶች ወይም የጦር ወንጀሎች ተጠያቂ የሆነውን አካል መለየት፣ የደረሰውን ጉዳት መጠን መወሰን፣ እውነትን ማረጋገጥ እና ፍትህን ማስፈንን ያጠቃልላል። ይህ በአጥፊዎች የተፈፀመውን በደል መቀበልን፣ ተጎጂዎችን መስማት እና እውቅና ማግኘት አስፈላጊ መሆኑን እና በቤተሰቦቻቸው እና በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘትንም ያካትታል።

ከላይ እንደተገለፀው የስርዓተ-ፆታ-ተኮር የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ እና ሂደት ሁለገብ መርሆዎችን በመጠቀም፣ የእውነት ፍለጋ ዘዴዎች በሴቶች እና ልጃገረዶች ላይ የሚደርሰውን የመብት ጥሰት ባህሪ እና ተፅእኖ ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው። በተለይም ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች (GBV) እና ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) ተጎጂዎችን በተለይም ሴቶችን እና የGBV እና CRSV ተጠቂዎችን በንቃት በማሳተፍ መተግበር አለባቸው። ፖሊሲው የእውነት ፍለጋ ሂደት በሴቶች ላይ ስለተፈጸሙት የመብት ጥሰቶች ዝርዝር ሁኔታ እንደሚያስፈልግና ሂደቱም በሴቶች ላይ ትርጉም ያለው ተፅእኖ እንደሚኖረው በግልፅ ቋንቋ ሊያመላክት ይገባል።

በኢትዮጵያ ሴቶች በማህበራዊ ህይወት ላይ በንቃት እንዳይሳተፉ አዘውትረው የሚያጋጥማቸውን መሰናክሎች ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ በተለያዩ የሽግግር ፍትህ ሂደቶች ውስጥ ተጎጂ ሴቶች እንዲመክሩበት ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል። ይህ ከሴቶች ጋር ለመመካከር ምቹ ሁኔታ መፍጠርን ማለትም የሴቶች መብት ተሟጋች ድርጅቶችን፣ ማህበራትን እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን በንቃት ማሳተፍ፤ እንዲሁም ስለእውነት ፍለጋ ምንነትና ሂደት በተለያዩ መንገዶች በሴቶች ዘንድ ያለውን ግንዛቤን ለማሳደግ መሰረታዊ ማህበራትን ማሳተፍ ይጠይቃል። የተጎጂዎችን የምስክር ቃል ከመሰነድ በፊት ምስጢራዊነትን ማረጋገጥ እና ይሁንታ ማግኘትን እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ እርምጃዎች ያካትታሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ እውነትን በመፈለግ ሂደት ውስጥ ለሚሳተፉ ሴቶች ደህንነታቸው የተጠበቁ ሁኔታዎች ማመቻቸት፤ በተለይም ደህንነቱ የተጠበቀ ማረፊያ ቦታዎችን ማዘጋጀት፤ የጥሪ ማዕከላትን ማቋቋም፣ የቅሬታ ማቅረቢያ ዘዴዎችን መቀየስ፣ ለልምድ መጋራት የሚበጁ የአቻ ድጋፍ፤ የስነ-ልቦና እና ማህበራዊ ድጋፍ አገልግሎቶችን መዘርጋት ሊያካትት ይችላል።

### በአማራጭ እውነት ፍለጋ ሂደቶች ላይ የሚቀርብ ግብረመልስ

ተጎጂን ያማከለ አካሄድ የሽግግር ፍትህ እውነትን የመፈለግ ሂደት እንደሚመራ “Green Paper” ይገልጻል። ምንም እንኳን ተጎጂን ያማከለ አሰራር ሁሉን አቀፍ እና አሳታፊነቱን ለማረጋገጥ ወሳኝ እንደሆነ ቢታወቅም የዳበረው ፖሊሲ ለሥርዓተ-ፆታ ትኩረት የሚሰቡ ዘዴዎችን ለእውነት ፍለጋ አቀራረቦች አይነተኛ ገጽታዎች አድርጎ መጠቀሙ ወሳኝ ነው።

እውነትን ከመፈለግ ሂደት አንፃር “Green Paper” ሁለት አማራጮችን አቅርቧል፡፡ አንደኛው የነባር ተቋማትን ማለትም የብሔራዊ ምክክር ኮሚሽን እና የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ስልጣንን ማሳደግ ወይም አዲስ እውነት አፈላላጊ ኮሚሽን ማቋቋም ናቸው።

ለICTJ እና NEWA ሀሳባቸውን የሰጡ ሴቶች አዲስ የእውነት አፈላላጊ ኮሚሽን መመስረት እንደሚያስፈልግ ያስቀምጣሉ: ይህውም የሥርዓተ-ፆታ ተኮር አቀራረብን ማዕከላዊነት እና ቢያንስ 30% የሴቶችን ተሳትፎ ለማረጋገጥ፤ በሁሉም ሂደቶች እና ውሳኔዎች ውስጥ ሥርዓተ-ፆታን ቀዳሚ ለማድረግ ያግዛል ብለው ያምናሉ፡፡ ይሁንና የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን የስልጣን ዘመኑን በማራዘም የበላይ ተከታታይ አካል ሆኖ በሂደቱ ውስጥ መሳተፍ ይኖርበታል።

## 5. ማካካሻዎችን በሥርዓተ-ፆታ ማካተት

ማካካሻ ማለት የትጥቅ ግጭት ወይም ፖለቲካዊ ብጥብጥ ባስተናገዱ አገሮች ውስጥ የሰብአዊ መብት ረገጣ እና የእኩልነት መጓደል የሚያስከትለውን መዘዝ እውቅና መስጠት ብሎም መጠገን ማለት ነው፡፡ በዚህም ርገድ “Green Paper” እንዲህ ይላል።

“... የዚህ ዘዴ ዋና አላማ የመፍትሄ ሂደቱን መደገፍ እና የተጎጂዎችን እና የአጥፊዎችን ባህሪ ማሻሻል ነው...”

የሰብአዊ መብት ጥሰት ሰለባ የሆኑ ሰዎች ሁሉ ፍትህ እና ካሳ የማግኘት መብት አላቸው። ተጎጂዎች የተለያዩ ፍላጎቶች ያላቸው ሲሆን እነዚያ ፍላጎቶች በጊዜ ሂደት ሊለወጡ እና የሚፈለገው የካሳ አይነት እንደ ተጎጂው አቅም፣ ጾታ፣ ዕድሜ እና ማህበራዊ ማንነት ሊለያይ ይችላል። ለምሳሌ ሴቶች ከወንዶች በተለየ መልኩ የሙብት ጥሰት ያጋጥማቸዋል፡፡ የሙብት ጥሰቱ በልምድ በፆታዊ-ጥቃት እና ውጤቶቹ ላይ ብቻ የተገደበ ሊሆን ኣይገባም።

ግልጽ የሆነ፣ ተለዋዋጭ እና ተጎጂዎችን ያማከለ የሽግግር ፍትህ ሂደት ለመፍጠር የሚመለከተው አካል ችግሮቻቸው እና ፍላጎቶቻቸው መሟላታቸውን ለማረጋገጥ ተጎጂዎችን ስለማንኛውም ማካካሻ ዕቅድና አተገባበር ላይ ማማከር ያስፈልጋል። ማካካሻን የሚመለከቱ ውስኔ አሰጣጦች ላይ ከላይ የተገለፀው የ30% የሴቶች ውክልና የሚያዘው ምርህ መከበር አለበት።

ማካካሻው ወይም የገንዘብ ክፍያ ከብዙ የተለያዩ የቁሳቁስ ማካካሻዎች ውስጥ አንዱ መሆኑን ማስታወስ ጠቃሚ ነው። ሌሎች የማካካሻ ዓይነቶች ደግሞ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶችን ማስከበር፣ የአካል ማገገሚያ እና የመሬት፣ የመኖሪያ ቤት፣ የጤና እንክብካቤ ወይም የትምህርት እድል መስጠትን ያካትታሉ። ማካካሻ በአስተዳደራዊ መርሃ ግብሮች (በአስተዳደራዊ ካሳ) ሊተገበር ይችላል፤ ወይም በሙግት ውጤት (በፍርድ ቤት የታዘዘ ማካካሻ) ሊተገበር ይችላል።

“Green Paper” ለኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ሊመጥኑ የሚችሉ ሁለት ማካካሻ ሞዴሎችን አስቀምጧል። አስተዳደራዊ ሞዴል “... የማካካሻ ኮሚሽኖች ሂደቱን እንዲመሩ እና እንዲያስተባብሩ፤ ተጠቃሚዎችን እንዲለዩ፣ የማካካሻ ዘዴዎችን እንዲነድፉ፣ እንዲሁም የማሻሻያ ዘዴዎችን እንዲቀይሱ ይመክራል ፡፡ ሁለተኛው አማራጭ ሞዴል ደግሞ የግለሰብ ካሳ እና የወንጀል ሂደቶችን በማጣመር እና የጋራ ካሳ ጉዳዮችን በብሔራዊ ውይይት ኮሚሽን ወይም በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን በኩል በማስተናገድ የሚደረግ የግለሰብ ካሳ ሂደት ነው።

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የሥርዓተ ፆታ እኩልነት እና የሀብት ተጠቃሚነት እንዲሁም ተያያዥ አሰራሮች ከፆታ አንፃር እጅግ የተዛነፉ በመሆኑ እንደ ሁለተኛ አማራጭ የሚታየው የፍርድ ቤት የግለሰብ ካሳ ክፍያ ውሳኔ ቢሆንም የሴቶች መደበኛ ፍርድ ቤቶች ተደራሽ ባለመሆናቸው የተነሳ የሴቶችን ፍላጎት በተሟላ መልኩ መመለስ አይችልም። ይህ ደግሞ በተለይ በድህነት በሚኖሩና እና በተገለሉ ሴቶች፣ የገቢ ምንጭ የሌላቸው ወይም ሀብት የማያስተዳድሩ፤ ወይም አድሎአዊ ድርጊቶች የሚፈፀምባቸው እና የህግ ከለላ የማያገኙ ሴቶችን ይመለከታል። “The Green Paper” ላይ ከቀረቡት ሁለት አማራጮች ውስጥ አስተዳደራዊ ካሳን በሚተገብረው እውነት ፈላጊ ኮሚሽን ስር ተፈናቃዮችን ያማከሉ ፕሮግራሞችና እና ሀብት አስተዳደር በሚል ልዩ ክፍል ቢዘረጋ የበለጠ ተደራሽነት ይኖረዋል ብለን እናምናለን። ይህ አዲሱ ህጋዊ አካል ሴቶች እና ልጃገረዶች ከሌላው በተለየ በግጭት ወቅት የሚደርስባቸውን የጥቃት አይነቶች መለየትና እውቅና መስጠት አለበት።

ተሞክሮዎች እንደሚያመለክቱት ከተለያዩ የማካካሻ ዓይነቶች መካከል ወደነበሩበት መመለስ፣ መልሶ ማቋቋም እና ማህበራዊ ድጎማ ለሥርዓተ-ፆታ አሰራር ተስማሚ ናቸው። እነዚህም በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ሥርዓታዊ እና መዋቅራዊ ጥቃት መንስኤዎችን በተሻለ መንገድ ለመፍታት ያስችላሉ።

የኢትዮጵያ “Green Paper” የሀብት ውስንነት አስተዳደራዊ ማካካሻዎችን እና ለሥርዓተ-ፆታ የሚስማሙ የካሳ አሰጣጦችን ለመተግበር እንቅፋት መሆናቸውን በሚገባ ይጠቅሳል። በፖሊሲው ተቀባይነት ያገኘው ተጎጂዎችን ያማከለ አሰራር እና መሰል አካሄዶች በሽግግር ፍትሃዊነት ላይ ያስከተሉትን አበረታች ለውጦች በማስመልከት አለም አቀፍ አጋሮችና ባለድርሻ አካላት አስፈላጊውን የገንዘብ እና የቴክኒክ ግብአት እንዲያቀርቡ እንዲሁም የኢትዮጵያ መንግስት ደግሞ ከፍተኛ የፖለቲካ ቁርጠኝነት እንዲያሳይ አሳስበዋል።

## 6. የወንጀል ተጠያቂነትን በሥርዓተ-ፆታ ማካተት

በወሲባዊ እና በፆታ ላይ የተመሰረቱ ወንጀሎችን በተመለከተ የወንጀል ክስ (SGBV) የኢትዮጵያን የውስጥ ህጎች እንዲሁም ኢትዮጵያ የተስማማችባቸውን አለም አቀፍ ህጎች እና ስምምነቶችን የሚያበረታታ እና የሚያስፈጽም አጠቃላይ የህግ ማዕቀፍ ያስፈልገዋል። በሀገሪቷ የፍትህ ስርአት ውስጥ የመረጃ ህግ የተሟላ አለመሆኑ ከSGBV ለተረፉት እና የጥቃት ሰለባዎች ፍትህ ለማዳረስ እንቅፋት መፍጠር የለባቸውም። በሌላ አነጋገር በኢትዮጵያ ነባሩ የወንጀል ህግ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረገውን እውነት ፍለጋ እና የወንጀል ተጠያቂነት ሂደትን ወሰን መገደብ የለበትም።

በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን የሚያካትቱ የሀገር ውስጥ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጎች በበቂ ሁኔታ የማያብራሩ ሲሆን ዓለም አቀፍ ሕጎች እና ስምምነቶች መጠቀስ አለባቸው። ICTJ እና NEWA ባደረጉት ምክክር መሰረት የሚመለከታቸው የመንግስት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እና ኤጀንሲዎች የወንጀል ፍትህ ሂደቶችን እንዲገመግሙ እና እንዲያሻሽሉ ተመክሯል፡፡

በተጨማሪም በኢትዮጵያ በቅርቡ በተከሰቱ ግጭቶች በሕይወት ለተረፉ እና ለተጎጂዎች ፍትህ ለማዳረስ ሲባል የብሔራዊ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ በበኩሉ የሴቶችን የጦርነት እና የግጭት ተሞክሮ ከጾታዊ ጥቃት ጋር ብቻ ከማመሳሰል እንዲቆጠብ እንዲሁም ጾታዊ ጥቃትን ወደ አስገድዶ መድፈር ወንጀል እንዳያሳንስ መጠንቀቅ ይኖርበታል። ይልቁንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተፈጠሩ ግጭቶች ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ያጋጠሟቸውን የተለያዩ አካላዊና ማኅበራዊ ጥቃቶች በተመለከተ መፍትሄ መስጠት ይኖርበታል። የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ፆታን መሰረት ያደረጉ የመብት ጥሰቶች ጥልቀት፣ ቅርፅ እና ውስብስብነት መገንዘብ አለበት። በሌሎች በርካታ አገሮች ውስጥ ያሉት ተመሳሳይ ፖሊሲዎች ይህንን ሁለገብ አካሄድ ይጠቀማሉ፡፡ ነገር ግን በተለየ ሁኔታ በጦርነት እና በግጭት ወቅት የሚፈፀሙ የመብት ጥሰት አይነቶችን በተመለከት የተለየ ይዘት ያለው መረጃ መሰብሰብን ያካትታል።

በቅርቡ በኢትዮጵያ ውስጥ በተከሰቱት ጦርነቶች እና ግጭቶች ውስጥ የታዩት በርካታ አይነት አካላዊ እና ማህበራዊ ጥቃቶች ምናልባትም አሁን ባለው የሀገር ውስጥ የወንጀል ህግ በበቂ ሁኔታ ሊዳኙ አይችሉም። ለአብነት ያህል በሴቶች የመራቢያ አካል ክፍሎች ውስጥ አደገኛ ባእድ ቁሶችን ማስገባት እና የቤተሰብ አባላት ፊት አስገድዶ መድፈር ወይም ሌሎች ፆታዊ ጥቃቶችን ያጠቃልላል። መሰል ዘግናኝ የመብት ጥሰት ሰለባዎች ቀሪ ህይወታቸውን የበለጠ አስከፊ ያደርገዋል። ሆን ተብሎ በሴቶች የመራቢያ አካላት ላይ

የተደረገው የሴቶችን ክብር ለመንጠቅ ብቻ የታሰበ ሳይሆን የመራባት አቅማቸውን በመቀነስ ብሔረሰቡ ያለውን የህዝብ ቁጥር ጭምር ለመገደብ ነው። በሌላ በኩል ቢጋምቤላ ክልል እንደታየው የመብት ጥሰት፣ ግጭትን ለማባባስና አንድን ጎሳ ለማዳከም ሆን ተብሎ ሴቶች ኢላማ ተደርገዋል። በቤኒሻንጉል ክልል ሰላም በማስፈን ስም ተፋላሚ ጎሳዎች ወጣት ልጃገረዶቻቸውን በመለዋወጣቸው ለባርነት ተዳርገው ነጻነትና ክብራቸው እንዲነፈግ ተደረጓል።

ፖሊሲው የወንጀል ህግን ማሻሻያ ከግምት ውስጥ ማስገባት፤ ወይም በግጭት ወይም በጦርነት ጊዜ የሚከሰት ወሲባዊ ጥቃትን ጨምሮ ለGBV መከላከል እና ምላሽ የሚሰጥ የGBV መርሀግብር ሊኖረው ይገባል።

## ማካተት ያለባቸውም ሀሳቦች

- በትጥቅ ግጭት እና በጦርነት ወቅት የሚፈጸሙ አካላዊ፣ ጾታዊ እና ስነ ልቦናዊ ጥቃቶችን ጨምሮ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን በግልፅ ማስቀመጥና ለመፍትሄውም ቁርጠኛ አቋም ማስቀመጥ።
- አካላዊ ጥቃት ስንል እንደ ድብደባ፣ የአካል ጉዳት የሚያስከትል ጥቃት ወዘተ እና ስነልቦናዊ/ስሜታዊ ጥቃት ማለትም እንደ ስድብ፣ ማንቋሸሽ፤ ዘለፋ ወዘተ ናቸው፡፡
- በግጭት/በጦርነት ወቅት የሚፈጸሙትን የGBV ወንጀሎች እንደ አባባሽ ሰበብ ተቆጥረው ከባድ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው ከግምት ውስጥ ማስገባት
- የማስረጃ ደንቦችን እና አፈጻጸማቸውን መከለስ፤ በወንጀል ሂደት ውስጥ የተጎጂዎችን እና ተከላካዮችን ፍትሃዊ የፍርድ ሂደት በተመለከተ እርምጃዎችን መውሰድ፣ የህግ ማስረጃዎችም ያለአግባብ ገዳቢ፤ ተቾካይ፣ ወይም በስርዓተ-ፆታ አመለካከቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ እንዳይሆኑ ማረጋገጥ።

ከግጭት ጋር የተያያዙ የSGBV ልዩ ባህሪያትን እና ተያያዥ ወንጀሎችን በቅርብ ጊዜ በኢትዮጵያ ከታየው የወንጀሎቹ ክፋት ሁኔታ ጋር በማገናዘብ የማስረጃው ክብደት በአዲስ የሽግግር ፍትህ ዘዴ በተያዙ የSGBV ጉዳዮች ላይ እንደገና እንዲገመገም እናሳስባለን። ለወንጀል ሰለባዎቹ ፍትህን በበቂ ሁኔታ ለማዳረስ የማስረጃው ሸክም የተረፉት ላይ ብቻ ሳይሆን በሙስና ጉዳዮች ላይ እንደሚደረገው በክሱም ላይ መሆን አለበት። በቅርብ ጊዜ በኢትዮጵያ ጦርነት እና ግጭት የተፈፀመውን ዘግናኝ የፆታ ጥቃት ከግምት ውስጥ በማስገባት በልዩ የሽግግር ፍትህ ክፍል ወይም በልዩ ፍርድ ቤቶች መስተናገድ አስፈላጊ ነው ብለን እናምናለን። ከጥቃት የተረፉ ሰዎችን የሕጻናትን እና የሴቶችን ልዩ ፍላጎቶች ለማሟላት በተዘጋጀው አዲስ የሽግግር ፍትህ ዘዴ/ተቋም ፍትህ እንዲሹ ለማበረታታት መተማመንን መገንባት በጣም አስፈላጊ ነው። የወንጀሎቹ ክብደት እና ውስብስብነት፣ ከአካባቢው ፍርድ ቤቶች የስራ ጫና እና የፖለቲካ ሁኔታ ውስብስብነት የተነሳ ለተጠቀሱት ዘግናኝ ወንጀሎች የተለየ የፍርድ ክፍል አስፈላጊ መሆኑን የበለጠ አጉልቶ ያሳያል።

ሁሉም ወንጀለኞች ሊከሰሱ እንደማይችሉ በመገንዘብ፤ የሽግግር ፍትህን ለማስፈን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ወንጀሎች መለየት አስፈላጊነትን በተመለከተ ICTJ እና NEWA ማንኛውም አይነት የSGBV ጉዳዮች ክስ ሊመሰረትባቸው እንደሚገባ የሚያረጋግጥ ፖሊሲ አስፈላጊነትን በመጠቆም እንደዚህ ባሉ አጋጣሚዎች ሁሉም ወንጀለኞች ሊከሰሱ እንደሚገባ ይመክራሉ።

በሴቶች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የጅምላ ንብረት ውድመት ሲከሰቱ መሰል ወንጀሎች ለህግ መቅረብ ያለባቸው ሲሆን ቀንደኛ ተዋናዮች ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት፡፡ በንብረት ላይ የሚደርሰው ጉዳት ሁል ጊዜም በአስተዳደራዊ ካሳ መስተካከል አለበት።

በመጨረሻም፣ የብሔራዊ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ወንጀለኞችን ለመለየት እና ወደፊት ሊጎዱ የሚችሉ ሰዎችን ለመጠበቅ የፆታዊ ጥቃት ወንጀለኞችን ዝርዝር ይፋ እንዲያደርግ እንመክራለን።

## 7. በተቋማዊ ማሻሻያዎች ውስጥ ሥርዓተ-ፆታን ማካተት

በሽግግር ፍትህ ሂደት ውስጥ ተቋማዊ ማሻሻያ ተጎጂዎችን እንደ ዜጋ እና የመብት ባለቤቶች መሆናቸውን ለማረጋገጥና በዜጎች እና በህዝባዊ ተቋሞቻቸው መካከል መተማመን ለመፍጠር ይተጋል፡፡ እንዲህ ዓይነቱን የተሐድሶ አቅጣጫ በሚገባ ተረድቶ፣ አሳታፊና ግልጽ በሆነ መንገድ ሲተገበር፣ የመካሻ ባህሪያት እንዳሉት ያንፀባርቃል።

በተቋማዊ ማሻሻያ ስር፣“Green paper” ሰራተኞችን እና ተቋማዊ ማሻሻያዎችን የማጣራት ግልፅ ስልት ይዘረዝራል። ይህ ስልት ሴቶች ልዩ ፍላጎቶች እና አመለካከቶች እንዳሏቸው አጽንኦት እና እውቅና የሚሰጥ ቋንቋ ማካተት አለበት። የፖሊሲው ትግበራ ለሴቶች በተለይም በድህነት የሚኖሩ፣ የተገለሉ ሴቶች፣ ልጃገረዶች እና ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃቶች (CRSV) ሰለባዎችን ተደራሽነት እና ደህንነት ማረጋገጥ አለበት።

በኢትዮጵያ በሽግግር ፍትህ ፖሊሲ (TJ) መሰረት የሚካሄደው ተቋማዊ ማሻሻያ ማካተት ካለባቸው ተግባራት መካከል የመብት ጥሰት የፈጸሙ ግለሰቦችን ከስልጣን ማሰናበት፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ወደ ተቋም በሀላፊነት ቦታ ላይ የሚመደቡ ባለሙያዎች ለሰብአዊ መብት፣ ለፍትህ እና ለጾታ እኩልነት ባላቸው ዕውቀትና ቁርጠኝነት (መዋቅራዊ ማጣራት) ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ ይገኙበታል ።

የሽግግር ማጣራት ተጎጂዎችን ያማከለ የሽግግር ፍትህ አካሄድ ወሳኝ አካል ሲሆን በተለይም ከፆታዊ ጥቃት ለተረፉ ሴት ተጠቂዎች ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ ይፈጥራል።

“በሶማሌ ክልል በከፍተኛ የፖለቲካ ደረጃ ላይ ያለው የክልሉ መንግስት ቁርጠኛ ነው፣ ተጨባጭ እርምጃም ወስዷል። ነገር ግን ምስክርነቴን ለመስጠት ወደ ፖሊስ ጣቢያው ስሄድ በጄል ኦጋዴን ውስጥ የነበረው ፖሊስ በክፍሉ ውስጥ ተቀምጧል። .

በሶማሌ ክልል አዲስ በተቋቋመው ኮሚሽን ክልላዊ እውነትና እርቅ ሂደት ተግባራዊ ለማድረግ በሂደት ላይ ያለ ቢሆንም ከላይ የተጠቀሱት አይነት ጉዳዮች ግን ያልተለመዱ አይደሉም፡፡ በደል የደረሰባቸው ሴቶች እንደተናገሩት ጥቃት ያደረሱባቸው አንዳንድ የፀጥታ ሀላፊዎች አሁንም በፌደራል እና በክልል ደረጃ በህግ አስከባሪ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ በስልጣን ላይ እንደሚገኙ ጠቁመዋል።

የሰራተኞች ማጣራትን በተመለከተ ማንኛውም ተቋማዊ ማሻሻያ ስርዓተ-ፆታን መተግበር እንዳለበት የሚጠቁም ግልጽ ቋንቋዎች ሊኖሩት ይገባል። ይህም የሴቶች ውክልና ዝቅተኛውን የ30% የኮታ መስፈርት ማሟላትን ጨምሮ፣ የሰው ሃይል ማፍራት እና የተጠናከረ የአቅም ግንባታን ያካትታል፡፡ በተጨማሪም የሰብአዊ መብት ጥበቃ እና የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ማስፈን፣ ህብረተሰባዊ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃ ግብሮች ማካሄድ፣ በክትትልና በግምገማ መለኪያዎች ውስጥ የተካተቱ የሥርዓተ-ፆታ አመለካከቶች የሥርዓተ-ፆታ አድሏዊነትን የሚከላከል የሥነ ምግባር ደንብ አስፈላጊነት መገንዘብ ያስፈልጋል።

## ማጠቃለያና ቁልፍ ምክረ ሀሳቦች

### 1. የፖሊሲው መርሆዎች እና ቋንቋ

በኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉን አቀፍ እና ጾታን ያማከለ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ለመዘርጋት እና ተግባራዊ ለማድረግ ግጭቶች እና ጥቃቶች በሴቶች ላይ የሚኖራቸውን ልዩ ትኩረት መገንዘብ አስፈላጊ ነው። ይህም ሴቶች የሚያጋጥሟቸውን ልዩ ተጋላጭነቶች እና የመብት ጥሰቶችን በተለይም ግጭት-ወለድ ወሲባዊ ጥቃቶችን በተመለከተ ልዩ ትኩረት የሚሻ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ይህ ፖሊሲ በአቀራረቡ ያልተቸነከረ እና ፈጠራን የሚጋብዝ ሆኖ፣ እንደ እድሜ፣ ጎሳ፣ አካል ጉዳተኝነት እና የተለያዩ የሴቶችን ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃዎችን ከግምት ማስገባት አለበት። በየደረጃው ያሉ ኢትዮጵያውያን ሴቶች የነቃ ተሳትፎ ማድረግ ወሳኝ ሲሆን በኮታ ላይ ብቻ ከመተማመን ይልቅ የአቅም ግንባታ እና ስልጠና ላይ አፅንዖት መስጠት በታሪክ ያለፊበትን የበደል አዙሪት የሚገታ ይሆናል፡
፡

በስርዓተ-ፆታ አለመመጣጠን ምክንያት ሴቶች በአገር አቀፍ ተቋማት እና በሽግግር የፍትህ እርምጃዎች ውስጥ ዝቅተኛ ውክልና አላቸው። ከላይ ከተጠቀሰው ንድፈ ሃሳብ ጋር በማጣጣም የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ በሁሉም ቁልፍ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች እና በሽግግር ፍትህዊ አካላት ውስጥ ያሉ የሰው ሃይል አባላት ቢያንስ 30% የሴቶች ውክልና ሊይዝ ይገባል።

ይህ አካሄድ ፍትሃዊ ውክልናን ከማረጋገጥ ባሻገር የሴቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ ያበረታታል። የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ እና ማዕቀፎች የሴቶች ውክልና ከ30%ቱ ኮታ በላይ አድርገው የሚሰሩ ፕሮግራሞችን ማበረታታትና ወደ ጾታ እኩልነት እንዲተጉ፤ በሂደትም ወደ 50/50 ከፍ እንዲሉ ማገዝ ይኖርበታል።

የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ የአካታችነት፣ ለሥርዓተ-ፆታ ስስነት እና የሥርዓተ-ፆታ ሁሉን አቀፍ ባህሪ ያለውና መርሆቹም ግልጽ በሆነ ቋንቋ እና ወጥነት ባለው መልኩ ሊገለጹ ይገባል። በተጨማሪም ሴቶች በተለየ ሁኔታ የሚጎዱባቸውን መንገዶች በማያሻማ መልኩ በማስቀመጥ ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ ይኖርበታል።

የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት የተቀመጡትን ግዴታዎች፣ እንዲሁም ቁልፍ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን፤ እና የክልል የሕግ ድንጋጌዎችን፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ የአፍሪካ ህብረት የሽግግር የፍትህ ፖሊሲን ዋቢ ማድረግ አለበት።

## 2. እውነትን መፈለግ

እንደ "የGreen Paper" አገላለፅ አዳዲስ ገለልተኛ ተቋማት ለሽግግር ፍትህ ኮሚሽኑ ማስታወቅ እንዳለባቸው ይጠቁማል። በአግባቡ የሰለጡኑ እና ልዩ ክህሎት ያላቸውን ሰራተኞች አስፈላጊነት ያጎላል፡፡ ይህ ፖሊሲ አዳዲስ ሀሳቦች በመቅረፅ ራሱን የቻለ የእውነት ኮሚሽን እንዲቋቋም ያበረታታል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ለሥርዓተ-ፆታ አካሄድ ስስ ስሜት በማሳየት ረገድ የጎላ ሚና ለመወጣት ስለሚያስችለው ነው።

ለዘላቂነት እና አቅም ግንባታ ሲባል የሽግግር ፍትህ ኮሚሽኑ ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ጋር የጠበቀ የስራ ግንኙነት እንዲፈጥር ይመከራል። EHRC ስልታዊ በሆነ መልኩ የሽግግር ፍትህን የክትትልና የግምገማ አውታሮች በተልእኮው ውስጥ ማካተት እና ማዋሃድ ይችላል።

## 3. ካሳዎች

ግልጽ፤ ተለዋዋጭ እና ተጎጂዎችን ያማከለ አካሄድን የተከተለ የሽግግር ፍትህ በፖሊሲው ቀረጻ፤ ትግበራ እና አፈፃፀም ምእራፎች ተጎጂዎችን በአግባቡ ማማከርን ያካትታል። በሂደቱም ሙሉ በሙሉ ሴት የጥቃት ሰለባዎችን ማሳተፍ እና ቢያንስ 30% የውሳኔ ሰጪነት ቦታዎችን በሴቶች ለመሙላት ቃል መግባት አስፈላጊ ነው።

በዚህ ስምምነት ላይ ከቀረቡት አማራጮች መካከል የአስተዳደር ማካካሻ ለሥርዓተ-ፆታ ትኩረት በመስጠትና በተለይም የጥቃት ሰለባ ሴቶችን በማካተት ረገድ ተመራጭ ነው፡፡ የተገለሉ ሴቶችን ለማካካስ የሚደረጉ ተግባራትን በአዲሱ እውነት አፈላላጊ ኮሚሽን ስር በማድረጉ ብቻ ሳይሆን በዚህ ስር በሚደራጀው የስደት ተመላሾች እና ሀብት አስተዳደር ክፍል ስር የእነዚህን ተጎጂዎች ጉዳይ መከታተሉ ብሄራዊ ፍ/ቤቶች ተደራሽ ባልሆኑባቸው ሁኔታዎች የሚከሰተውን ችግር ለመቅረፍ ያግዘዋል፡፡

ይህንን ሞዴል መተግበር በቂ ሀብቶችን ይጠይቃል፡፡ ለስኬታማነቱም የኢትዮጵያ መንግስት ከፍተኛውን የፖለቲካ ቁርጠኝነት ማሳየት ሲኖርበት አለም አቀፍ አጋሮች እና ባለድርሻ አካላት በበኩላቸው አስፈላጊውን የገንዘብ እና የቴክኒክ ግብአት በማቅረብ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው፡፡

## 4. የወንጀል ፍትህ እና ለፆታዊ እና በፆታ–ተኮር ጥቃት ሰለባዎች ልዩ ጥበቃ በተመለከተ

በወሲባዊ እና በፆታ-ተኮር ጥቃቶች የወንጀል ክስ (SGBV) በተመለከተ የኢትዮጵያን የውስጥ ህጎች እንዲሁም ሀገሪቷ የተስማማችባቸውን አለም አቀፍ ህጎች እና ስምምነቶች የሚያበረታታ እና የሚያስፈጽም አጠቃላይ የህግ ማዕቀፍ ያስፈልገዋል።

CRSV እና GBV በግጭት ሂደት ውስጥ በልዩ ሁኔታ መታየት አለባቸው። የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥሰቶችን ስፋት፣ ቅርጾችን እና ውስብስቦቹን ከግምት ማስገባት አለበት።

የጅምላ የንብረት ውድመት ካለው ከባድ አሉታዊ ተጽእኖ አንጻር፣ ሁሉም የSGBV እና የንብረት ጉዳት ጉዳዮች ያለ ምንም ይቅርታ ለፍርድ እንዲቀርቡ እንመክራለን። ነገር ግን SGBV በተመለከተ ሁሉም ወንጀለኞች መካተት ሲገባቸው በጅምላ ንብረት ላይ ጉዳት ሲደርስ ግን ዋና ዋና የጥቃቱ ፈጻሚዎችን ብቻ ማካተት አለባቸው። በተመሳሳይ መልኩ ማንኛውም ከSGBV ጋር በተገናኙ የተጠረጠሩ ወንጀለኞች ምህረት ማግኘት የለባቸውም።

## 5. ተቋማዊ ማሻሻያ

ማንኛውም ተቋማዊ ማሻሻያ ሥርዓተ-ፆታዊ ምልከታን ከግምት ያስገባ መሆን አለበት፣ ይህንንም የያዘ መርህ በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ውስጥ መካተት አለበት።

በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ መሠረት የሚደረግ ተቋማዊ ማሻሻያ ማካተት ካለበት ግዴታዎች መካከል የሙብት ጥሰት የፈጸሙ ግለሰቦችን ከሃላፊነታቸው ማንሳት፤ እንዲሁም ወደ ተቋማት ለህላፊነት የሚመደቡ ባለሙያዎች ለሰብአዊ መብት፣ ለፍትሕ፣ ለጾታ እኩልነት እና ተያያዥ ጉዳዮች ባላቸው እውቀትና ቁርጠኝነት መሆኑን ማረጋገጥ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

በተቋማዊ ማሻሻያው መሰረት የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከሆኑት በተለይም የሴቶች መብት ተሟጋች ድርጅቶች ጋር ተጋላጭ እና የተገለሉ ሴቶችን በተመለከተ በቅርበት ለመስራት የሚያስችል ግልፅ ተልዕኮዎችንና እና ሚናዎችን ማካተት አለበት።

## 6. መተማመንን መፍጠርና ምቹ አካባቢን በመገንባት

የሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ግልፅነት ያላቸውን ፖሊሲዎችን ነድፎ ለተፈፃሚነታቸው መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል። የኢትዮጵያ መንግስት በበኩሉ በስርዓተ-ፆታ እና የሴቶች ሰብአዊ መብት አያያዝ ላይ በሌሎች የመንግስት መዋቅሮች እና ተቋማት ውስጥ ቆራጥ እርምጃዎችን በመውሰድ ጥረቱን በእጥፍ ሊያሳድግ ይገባዋል። ለምሳሌ አዳዲስ የፖሊሲ ማዕቀፎችን እና የድርጊት መርሃ ግብሮችን ትግበራ ማፋጠን እና ማጠናቀቅ ይጠበቅበታል፡፡ የሀገር አቀፍ የሴቶች ፖሊሲ፣ ብሄራዊ ፀረ- GBV ፖሊሲ እና በመረቀቅ ላይ ያለው የሴቶች፣ የሰላም እና የጸጥታ ብሄራዊ የድርጊት መርሃ ግብር የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ስርዓተ-ፆታን በሚደግፍ መልኩ እንዲተገበር ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ።

******

ይህ ሰነድ የተዘጋጀው በአውሮፓ ህብረት እና በሲቪል ሰላም አገልግሎት (CPS)፣GIZ የገንዘብ ድጋፍ ነው። የዚህ ሰነድ ይዘት የNEWA እና ICTJ ብቸኛ ሃላፊነት ስሆን በምንም አይነት ሁኔታ የሲቪል ሰላም አገልግሎት (CPS)፣ GIZ ወይም የአውሮፓ ህብረት አቋምን የሚያንፀባርቅ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም።

ICTJ Justice Truth Dignity

Co-funded by the European Union